# በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገሪቱ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ የሚፈቅደውን መመሪያ በሚመለከት የተዘጋጀ መግለጫ

## 1. መግቢያ

ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን ለመቀነስ እንዲያስችል ሆኖ የተነደፈውን የልማት ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ፋይናንስንና የክፍያ ሚዛንን የተመለከተ የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች ሲወስድ ቆይቷል:: ከነዚህ ውስጥ የወሊድና የውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጦች፣ የከረንት አካውንት ቁጥጥርን ማላላት (Current account liberalistion) እና የባንክና የኢንሹራንስ ዘርፍን ለኢትዮጵያዊያን ኢንቨስተሮች ክፍት ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው::

ስዚህ አኳያ የአገራችንን ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በማጠናከር ድህነትን ለመቀነስ ለሚደረገው ርብርብ በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያንም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ እና በአዋጅ ቁጥር 270/94 ኢትዮጵያዊ ተወላጅ መሆናቸውን የሚገልጽ ወቅቱ ያላለፈበት መታወቂያ ያላቸው የውጭ ዜጎች በሀገር ልማት እንቅስቃሴው ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገሪቱ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ መንግሥት ፈቅዷል:: ከዚህ በመቀጠል በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገሪቱ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ መፍቀድ የሚያስገኘው ተጨባጭ ውጤት እንዲሁም ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀው መመሪያ (Directive) ያካተታቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ ለማቅረብ ተሞክሯል::

2. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገሪቱ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ መፍቀድ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት

ኢትዮጵያ በውጭ አገር የሚኖሩ በርካታ ዜጎች ካላቸው አገሮች ተርታ የምትመደብ ቢሆንም በአስካሁኑ እንቅስቃሴ ከዜጎቿ ሊገኝ የሚችለውን የውጭ ምንዛሪ፣ ኢንቨስትመንት፣ የማኔጅመንትና የቴክኒክ ዕውቀት በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም ረገድ ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ ውጤት ሳታገኝ የቆየች መሆኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በዚሁ ጉዳይ ላይ ያካሄደው ጥናት አረጋግጧል። ጥናቱ እንደሚያሳየው ብዙ ታዳጊ አገሮች በውጭ ለሚኖሩ ዜጎቻቸው በየሀገሮቻቸው ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ በመፍቀድ የሚከተሉትን ጥቅሞች ለማግኘት ችለዋል።

- የክፍያ ሚዛን ጉድለትን ከማቃለልም በላይ አስተማማኝ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እንዲኖር ማድረግ፣
- የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ፣
- ለውጭ ምንዛሪ ምጣኔና ዋጋ መረጋጋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ እና
- የማኔጅመንትና የቴክኒክ እውቀት ፍሰትን በማመቻቸት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ የማይናቅ አስተዋፅኦ ማድረግ።

የበርካታ አገሮችን ልምድ ጨምሮ የዳሰሰው ይህ ጥናት በሀገር ውስጥ የሚገኙ ባንኮችን ሊአይዲቲ ያገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ለመክፈት ያላቸው ፍላጐት፣ የአገር ውስጥ ባንኮች ሥራውን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን ያላቸው የቴክኖሎጂና የሰው ሀይል አቅም፣ እና የሥርዓቱ ተግባራዊ መሆን በባንኮች የውጭ ምንዛሪ አቋም ላይ እና በጥቁር ገበያው የምንዛሪ ምጣኔ ላይ ያለው እንደምታና የመሳሰሉትን በስፋት ዳሷል።

3. በመመሪያው የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች

3.1 ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

የሚከተሉት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ ሊከፍቱ ይችላሉ።

ሀ/ በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ ፓስፖርትና በአግባቡ የተሞላና የተፈረመ ማመልከቻ ፎርም የሚያቀርቡ፣

በመመሪያው ተመልክቷል:: ነገር ግን በግንባር ቀርበው ሂሳቡን ለመክፈት የማይችሉ ግለሰቦች ሂሳብ ለመክፈት የሚጠይቁ መረጃዎቻቸውን በአቅራቢያቸው ለሚገኘው ኢምባሲ ወይም በአቅራቢያቸው ኤምባሲ ከሌለ በአካባቢያቸው ላሉት የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በማቅረብ እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ ያስፈልጋል::

## 3.5 ገንዘብ ወደ ውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚተላለፍበት ሁኔታ

➢ ወደ ውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚገባው ገንዘብ ከውጪ አገር የመነጨ መሆን አለበት:: ስለዚህ ገንዘቡ ቀጥሎ በተመለከቱት መንገዶች ብቻ መተላለፍ ይኖርበታል::

1ኛ. ከውጭ አገር በቀጥታ በባንክ በኩል በሚደረግ ሃዋላ (Direct Crediting)፣

2ኛ. ምንጩ ከሀገር ውጭ በሆነ የመንገደኞች ቼክ፣ (travelers check) (ለዚህም ማስረጃ ያለው መሆን አለበት)

3ኛ. በጥሬ ገንዘብ ከሆነ ገንዘቡ ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ወቅት ለጉምሩክ ያሳወቀበት (declare ያደረገበት) ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

4ኛ. ከውጭ አገር የመነጩ ልዩ ልዩ ቼኮች፣

5ኛ. በሀገር ውስጥ ባንኮች ካሉ ከሌሎች የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች የሚደረግ ትራንስፈር::

## 3.6 በውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ አጠቃቀምን (Use of the Account) በተመለከተ

➢ በውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ቀጥሎ ለተመለከቱት ተግባራት ለማዋል ይቻላል::

- በአገር ውስጥ በብር ለሚከፈሉ ክፍያዎች፣
- ወደ ሌሎች የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ለማስተላለፍ፣
- ለገቢ ንግድና ለሌሎች የውጭ የአገልግሎት ክፍያዎች (imports and foreign service payments)፣
- ወደ ውጭ አገር ትራንስፈር ለማድረግ፣
- በገበያ ላይ ባለው የምንዛሪ ምጣኔ መሠረት ወደ ብር ሂሳብ ለማስተላለፍ፣
- የባንክ አገልግሎት ክፍያን ለመፈፀም::

### 3.7 ለውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የሚከፈል ወለድን በተመለከተ

- በመመሪያው መሠረት የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ (fixed foreign currency deposits) ወለድ የሚከፈልበት ሲሆን የተንቀሳቃሽ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ (current foreign currency deposits) ግን ወለድ አይከፈልበትም::

- የሚከፈለው ወለድ ባንኮች በውጭ አገር ካላቸው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ (correspondent account) ከሚያገኙት ወለድ 50 በመቶ የሚሆነውን መጠን እንዲሆን የተመለከተ ሲሆን፣ በጊዜ ገደብ የተቀመጠ ሂሳብ ከ6 ወራት በፊት ወጪ ከተደረገ ግን ወለድ አይከፈልበትም::

### 3.8 የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወደ ብር ሂሳብ እንዲቀየር የሚያስገድዱ ሁኔታዎችና የውጭ ምንዛሪ ሂሳብን በሚመለከት የተከለከሉ ተግባራት

- የውጭ ምንዛሪ ሂሳብን ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ከሌሎች መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ (consistent) እንዲሆን ለማድረግ እንዲሁም ለሕገወጥ እንቅስቃሴዎች በር የሚከፍቱ አሠራሮችን ለማስቀረት በማሰብ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ወደ ብር ሂሳብ ስለሚቀየርበት ሁኔታና ክልክል ስለሆኑ ተግባራት የሚጠቁሙ አንቀጾች በመመሪያው ተካተዋል:: በዚህም መሠረት አንድ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የከፈተ ውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊም ሆነ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻውን ወደ ኢትዮጵያ ከቀየረ የውጭ ምንዛሪ ሂሳቡ ወደ ብር ሂሳብ እንዲቀየር መመሪያው ያዛል:: የጊዜ ገደባቸው ያልደረሱ ተቀማጭ ሂሳቦች ብቁ እስኪሆኑ (mature እስኪያደርጉ) ድረስ ተጠብቀው ወደ ብር ሂሳብ እንዲቀየሩ ይደረጋል::

- ቀጥሎ የተመለከቱት ተግባራት ክልክል መሆናቸው በመመሪያው ተመልክቷል::

  - ከውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችም ሆነ ከሌሎች የሀገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ምንጮች የተገዛን የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ለመክፈት ወይም ወደ እነዚህ ሂሳቦች ገቢ በማድረግ መጠቀም አይቻልም::

- የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ባላቸው ግለሰቦች ተጽፈው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ እንዲከፍቱ ላልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ተከፋይ እንዲሆኑ የሚያዙ ቼኮች ተከፋይ የሚሆኑት በብር ብቻ ይሆናል::

## 3.9 መመሪያውን በተላለፉ ባንኮችም ሆኑ ግለሰቦች የሚወሰድ እርምጃ

ማንኛውም ባንክ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን አንቀጾች ከተላለፈ የባንክን ሥራ ለመፍቀድና ለመቆጣጠር በወጣው መመሪያ ቁጥር SBB/27/2001 መሠረት ይቀጣል::

ማንኛውም የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ የከፈተ ደንበኛ መመሪያውን ተላልፎ ቢገኝ ሂሳቡ የተከፈተበት ባንክ ወዲያውኑ ሂሳቡን በዝግ ሒሳብ በማቆየት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ ይኖርበታል::